# የኢትዮጵያ የምግብ፣ መድኃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

## የትምባሆ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 771/2013

መጋቢት 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

**መግቢያ**

ትምባሆን ማጠቀም እንደካንሰር፣ የመተንፈሻ አካል ህመም፣ የልብ፣ በጭንቅላት ወስጥ የደም መፍሰስ እና ሌሎች ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች አጋላጭ ምክንያት እንደሆነ፣ እንዲሁም የአካል ጉዳት እና ሞት እንደሚያስከትል በሳይንስ የተረጋገጠ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ የትምባሆ ተጠቃሚ እና የወጣቱ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ የወጣቱን ተጋላጭነት ማጠበቅና በአግባቡ ቁጥጥር ካልተደረገበት የበለጠ እየጨመረ የሚሄድና የጤና ሚታወክ በማስከተል የዜጎች የህክምና ወጪ እንዲጨምርና አገሪቱ ለመድኃኒት ግዢ የምታወጣው ወጪና የውጭ ምንዛሬ ከፍተኛ በማድረግ፤ ምርታማነትን በመቀነስና ማህል ጉዳት በማድረስ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና እየፈጠረ የሚገኝ በመሆኑ፤

ትምባሆ ቀጥተኛ ተጠቃሚው ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት ባለፈ ለጭሱ የተጋለጡ ሰዎችን ጤና የሚጎዳ በመሆኑ፤ ለህዝብ ክፍት የሆኑ ቦታዎችና የሥራ ቦታዎች ከትምባሆ ጭስ ነጻ እንዲሆን ለማድረግ አፈጻጸሙን ማጠናከር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የምግብ እና መድኃኒት ባለስልጣን በምግብ እና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 71 ንኡስ አንቀጽ (2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የትምባሆ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 771 /2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ወስጥ: -

1) **"አዋጅ"** ማለት የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 ነው፤
2) **"ልዩ ፈቃድ"** ማለት የትምባሆ ምርት ወይም ጥሬ ዕቃ የማምረት፣ ወደ አገር ወስጥ የማስገባት፣ ወደ ውጭ አገር የመላክ ወይም በጅምላ የማከፋፈል ስራ ላይ ለሚሰራ ሰው የቁጥጥር ስርዓትና ማስፈርት ማስረት በማድረግ በባለስልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
3) **"ይዘት"** ማለት ትምባሆን ጨምሮ የትምባሆ ምርት ግብአት፣ ግብአቱን ለማምረት የሚጠቅሙ ንጥረ-ነገሮች፣ ጭማቂዎች፣ ለዝግጅት የሚያግዙ ነገሮች፣ ትምባሆ ወስጥ የሚገኝ ቅሪት፣ እና ከማሸጊያው ወደ ትምባሆ ምርቱ የሚገባ ንጥረ-ነገር ነው፤
4) **"ማጨስ"** ማለት የተለኮሰ ሲጋራ መያዝ ወይም የሲጋራ ጭሱን በትንፋሽ ወደ ወስጥ መሳብ ወይም ወደ ውጭ ማስወጣት ሁኔታ ወይም እነዚህ ሚዲጸም ነው፤ **"ከበር መለስ"** ማለት የተሰራበት ቁሳቁስ አይነት እና መዋቅሩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ መሆኑ ሳይወሰነው ማንኛውም በጣሪያ የተሸፈነ እና አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ግድግዳ የተከለለ ስፍራ ሲሆን በረንዳን ጨምሮ ነው፤
5) **"ባለስልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤
6) በአዋጁና በሚወጣው ደንብ ትርጉም የተሰጣቸው ሆነው በዚህ መመሪያ ወስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጋት በአዋጁ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

**3. የባለስልጣኑ ተግባር**

1) የባለስልጣኑ ተግባር:-

ሀ) የትምባሆ ምርትና ጥሬ ዕቃ ማምረት፣ ማስመጣት፣ በጅምላ ማከፋፈል እና ማላክ ስራ ልዩ ፈቃድ ማስጠትና መቆጣጠር፤

ለ) በፌደራል መንግስት ቁጥጥር በሚገባቸው ተቋማትና አገልግሎት ትምባሆ ማጨስ፣ማጠቀም፣እና መሸጥ ክልከላን መቆጣጠር፤

ሐ) በፊደል ሀ እና ለ በተመለከቱ ተቋማትና አገልግሎት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የትምባሆ ቁጥጥር ህጎችን ማስፈጸም፣

መ) ህገ-ወጥ የትምባሆ ምርት ቁጥጥር ማድረግ

ነው፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ የክልል ጤና ተቆጣጣሪ አካላት በክልሉ የሚከናወኑ የትምባሆ ቁጥጥር ተግባራትን ለማጠናከር አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ እንዳስፈላጊነቱም የትምባሆ ቁጥጥር ስራዎችን በትብብር ይሰራል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የትምባሆ ምርት ልዩ ፈቃድ አሰጣጥ

### 4. ስለልዩ ፈቃድ አሰጣጥ

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ መሰረት የትምባሆ ምርት ልዩ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2) ማንኛውም ሰው በትምባሆ ምርት ወይም ጥሬ ዕቃ ማምረት፣ ወደ አገር ወስጥ ማስገባት፣ ማላክ፣ ወይም ጅምላ ማከፋፈል ንግድ ስራ ላይ ከማሰማራቱ በፊት ልዩ ፈቃድ ከባለስልጣኑ ማግኘት አለበት፡፡

3) ማንኛውም ሰው ልዩ ፈቃድ ከባለስልጣኑ ለማግኘት በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ሁኔታዎችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

4) ልዩ ፈቃድ በስራው ዓይነት ማምረት፣ ጅምላ ለማከፋፈል፣ ማላክ ወይም ወደ አገር ወስጥ ማስገባት በሚል ለእያንዳንዱ ተነጣጥሎ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ይህ ሁኔታ የትምባሆ አምራች ያመረተውን ምርት ለጅምላ አከፋፋይ ማስረከብ በተመለከተ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

5) ማንኛውም ሰው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የትምባሆ ምርት ንግድ ስራ ለመስራት የፈለገ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) መሰረት ልዩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡ ሆኖም ልዩ ፈቃዱ በአንድ የልዩ ፈቃድ ሚረጋገጫ ሰነድ ተጣምሮ ሊሰጥ ይችላል፡፡

### 5. ልዩ ፈቃድ ስለመጠየቅና መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች

1) ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ለትምባሆ ስራ ልዩ ፈቃድ ለማግኘት ባለስልጣኑ ባስቀመጠው የማጠየቂያ ስርዓት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ጥያቄ ያቀረበ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መረጃዎች ማሟላት አለበት፡፡

   ሀ) የልዩ ፈቃድ አመልካቹ ሰው ስምና አድራሻ፣

   ለ) የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ስምና አድራሻ፣

   ሐ) ልዩ ፈቃዱ የሚጠየቅበት የትምባሆ ምርት ስራ ዓይነት ማለትም ማምረት ወይም ማስመጣት ወይም በጅምላ ማከፋፈል ወይም ማላክ፣

   መ) የተጠየቀበት ቀን፤ እና

   ሠ) በማጠየቂያ ስርዓቱ የተቀመጡ ሌሎች መረጃዎች፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርብ ጥያቄ የሚከተሉትን ሰነዶች በአባሪነት መያዝ አለበት፡፡

ሀ) ግለሰብ ነጋዴ ሲሆን የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ቅጂ፤ ድርጅት ሲሆን የተቋቋመበት ሰነድ ቅጂ፣

ለ) ሥራው የሚከናወንበት ቦታ የልዩ ፈቃድ ጠያቂው ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ወይም በክራይ ከሆነ የጸና የክራይ ውል ቅጂ፤

ሐ) የአገልግሎት ክፍያ መከፈሉን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ፣ እና

መ) የትምባሆ ስራ በሞኖፖሊ ተይዞ ባለበት ወቅት እንደሆነ የሞኖፖል መብት ያለው ሰው የሰጠው ፈቃድ ወይም የተስማማ ስለመሆኑ የሚገልጽ ሰነድ ቅጂ፣

ሠ) አመልካቹ የሞኖፖል መብት ያለው ሰው እንደሆነ የሞኖፖል መብት ስምምነት የተረጋገጠ ቅጂ እና

ረ) በማጠየቂያ ስርዓቱ የሚጠየቁ ሌሎች ሰነዶች፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ጥያቄ ያቀረበ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡፡

ሀ) በቂ ማከማቻ፣

ለ) በዚህ መመሪያ መሰረት ለባለስልጣኑ በመደበኛ መቅረብ ያለባቸው ወይም ባለስልጣኑ ሲጠይቅ እንዲቀርቡ የሚፈለጉ ሚጃዎችን መያዝ የሚያስችል የሰነድ አያያዝ ስርዓት፣ እና

ሐ) የስራ ቦታው ወይም ማከማቻው አግባብነት ባለው ህግ የሚጠየቁ የአከባቢ ጥበቃ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

## 6. ስለልዩ ፈቃድ ማረጋገጫ

1) ባለስልጣኑ ለልዩ ፈቃድ የቀረበ ማመልከቻን ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ ተገቢው ሁኔታ መሟላቱን በማረጋገጥ የልዩ ፈቃድ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ሚጃዎች ይይዛል፡፡

ሀ) ልዩ ፈቃዱ የተሰጠው ድርጅት ስምና አድራሻ፤

ለ) ልዩ ፈቃዱ የተሰጠበት የስራ ዓይነት፤

ሐ) ልዩ ፈቃዱ የተሰጠበት ቀን፤

መ) ልዩ ፈቃዱ የሚያበቃበት ቀን፤ እና

ሠ) ፈቃዱን ያጸደቀው ኃላፊ ስምና ፊርማ፡

3) በባለስልጣኑ የተሰጠ ልዩ ፈቃድ ድርጅቱ ስራውን በሚያከናውንበት ቦታ በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡

## 7. ልዩ ፈቃድን ስለማደስ

1) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሰረት የተሰጠ ልዩ ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

2) ልዩ ፈቃድ የሚታደሰው ፈቃዱ የተሰጠበት ጊዜ ለማጠናቀቅ ሁለት ወር ሲቀረው ጀምሮ ባለው ጊዜ ይሆናል፡፡

3) ልዩ ፈቃድ የሚታደሰው፡ -

ሀ) ባለልዩ ፈቃዱ ጥያቄ ሲያቀርብ፣

ለ) በባለስልጣኑ የሚጠየቁ ሚጃዎችን ሲያቀርብ፣

ሐ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ (4) የተመለከተው ሁኔታ ተሟልቶ ያለ እንደሆነ፤ እና

መ) አስፈላጊውን ክፍያ የፈጸመ እንደሆነ ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት ያልታደሰ ልዩ ፈቃድ በደንብ በተወሰነው የገንዘብ መቀጮ የልዩ ፈቃዱ ጊዜ ካበቃበት እስከ ሁለት ወራት ባለው ጊዜ ወስጥ ለማሳደስ ይቻላል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) በተጠቀሰው ጊዜ ወስጥ ያልታደሰ ልዩ ፈቃድ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) በተጠቀሰው በቅጣት የማስደሻ ጊዜ ወስጥ እያለ ፈቃዱ ሳይታደስ ወይም በቅጣት የማስደሻ ጊዜው በማለፉ የተሰረዘ እንደሆነ ልዩ ፈቃዱ የተሰጠበትን ስራ ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

7) በንኡስ አንቀጽ (5) መሰረት ልዩ ፈቃዱ የተሰረዘበት ሰው በቅጣት ከማስደሻ የሚጨረሻው ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ወስጥ በማንኛውም የትምባሆ ንግድ ስራ ለመሰማራት አይችልም፡፡

## 8. የትምባሆ ምርት ይዘት እና ተያያዥ ሚረጃን ይፋ ማድረግ

1) ማንኛውም የትምባሆ ምርት አምራች ወይም አስመጪ በትምባሆ ምርት ወስጥ ያሉትን ይዘቶች፣ እያንዳንዱን የትምባሆ ምርት አይነት እና ነጠላ ምርቱን፣ በብራንድ ግንድ ወስጥ ስላሉ እያንዳንዱን የብራንድ ምርቶችን ለማምረት ጥቅም ላይ የዋሉትን ይዘቶች በተማከተ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው ቅጽ 1 መሰረት ለባለስልጣኑ ሚረጃውን ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ስለድርጅቱ አጠቃላይ ሚረጃ፣ ስለትምባሆ ምርቱ ወይም ልቀቱ፣ የሽያጭ ሚረጃ፣ እና የምርቱን ወሀድ፣ ኬሚካል፣ ጎጂ ባህሪያት እና የታወቁ ወይም የተለዩ ቅንጣዮች የተማከቱ ተጨማሪ ሚረጃዎችን እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት የሚቀርብ የትምባሆ ምርት ይዘት በተለይም የምርቱ ወሀድ፣ ጎጂ ባህሪያት፣ የኒኮቲንና ኬሚካሎች መጠን ተቀባይነት ባለው በሶስተኛ ወገን ላብራቶሪ የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

## 9. ስለይዘትና ልቀት ገደብ

1) የትምባሆ ምርት ይዘት እና ልቀት ባለስልጣኑ ከሚያስቀምጠው መጠን በላይ መሆን የለበትም፡፡

2) ባለስለጣኑ የትምባሆ ምርት ይዘትና ልቀት ገደብ መጠንን ተግባራዊ ለማድረግ ለፈጻሚዎች በቂ የማሻጋገሪያ ጊዜ መስጠት አለበት፡፡

## 10. ናሙና ስለማሰባሰብ እና ሚፈተሽ

1) ባለስልጣኑ ለቁጥጥር ዓላማ ወይም ልዩ ፈቃድ ለመስጠት ዓላማ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የትኛውንም የትምባሆ ምርት ናሙና ከማምረቻ ቦታ፣ ከመጋቢያ ኬላ፣ ከመሻጫ ስፍራ፣ ተከማችቶ ካለበት ቦታ ወይም ምርቱ በህጋዊም ሆነ በህገ-ወጥ መንገድ ከሚገኝበት ቦታ እና ሰው ላይ ለመውሰድ ይችላል፡፡

2) ባለስልጣኑ በንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሰበሰበውን ናሙና ወይም ለልዩ ፈቃድ የቀረበ ናሙና ሲኖር የትምባሆ ምርቱን በራሱ ወይም ዕውቅና ባለው የሶስተኛ ወገን ላብራቶሪ እንዲፈተሽና እንዲለካ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3) በምርመራ የትምባሆ ምርቱ ወይም ግብዓቱ ከተፈቀደ ይዘት ውጭ ወይም መጠን በላይ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የምርቱ ባለቤት የምርመራውን ወጪ እንዲሸፍን መደረግ አለበት፤ ከዚህ ውጭ ላለሁኔታ የላብራቶሪ ፍተሻ ወጪውን ባለስልጣኑ የምርቱን ባለቤት እንዳስፈላጊነቱ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 11. የትምባሆ ምርት ወደ አገር ወስጥ ስለማስገባት

1) የትምባሆ ምርት ወይም ጥሬ ዕቃን ወደ አገር ወስጥ ማስገባት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ልዩ ፈቃድ ያለው ሰው ብቻ ነው፡፡

2) የትምባሆ ምርት ወይም ጥሬ ዕቃ ወደ አገር ወስጥ እንዲገባ የሚፈቀደው፡-

ሀ) አስመጪው ልዩ ፈቃዱን ሲያቀርብ፣

ለ) እንዳግባበነቱ በምርቱ ላይ ተፈጻሚ የየሚሆኑ የጤና ማስጠንቀቂያ፣ ገላጭ ጽሑፍ፣ የይዘት ማስፈርቶች እና ሌሎች በህግ የሚጠየቁ ማስፈርቶችን ያሟላ ሲሆን፣

ሐ) የምርቱ ስሪት አገር፣ የምርት መጠን፣ እና ተያያዥ ሚረጃዎች ተሟልተው ሲቀርቡ እና

መ) ምርቱ በዚህ ንኡስ አንቀጽ በፊደል (ሐ) መሰረት በቀረበው ሰነድ መሰረት የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

3) የትምባሆ ምርትን ለግል ፍጆታ ወደ አገር ወስጥ ይዞ መግባት የሚፈቀደው በግምሩክ ኮሚሽን በተወሰነው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

4) ማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ኒኮቲን ማስጫ መሳሪያ ወይም ሌላ ከሲጋራ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የቴክኖሎጂ ምርት ለግል ፍጆታ ወደ አገር ወስጥ ይዞ መግባት የሚቻለው አንድ ፍሬ ብቻ ይሆናል፡፡ ከአንድ ፍሬ በላይ የሆነ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 46 (2) እንደተደነገገው ለንግድ ዓላማ እንደሆነ ተቆጥሮ የሚወረስ ይሆናል፡፡

5) በአዋጁ አንቀጽ 49 ንኡስ አንቀጽ (5) መሰረት የሺሻ ምርትን ሆነ የሺሻ መጠቀሚያ ቁስን በማንኛውም መጠን ቢሆን ወደ አገር ወስጥ ይዞ መግባት የተከለከለ ነው፡፡

6) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3)፣ (4) እና (5) ን በሚቃረን ወደ አገር ወስጥ የገባ ምርት ተወርሶ ይወገዳል፡፡ የጥሰቱ ፈጻሚ አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡

## 12. ህገ-ወጥ የትምባሆ ምርትን ስለመቆጣጠር

1) ባለስልጣኑ በየወቅቱ ህጋዊ የትምባሆ ምርቶችን ስም ለተቆጣጣሪ አካላት ያሳውቃል፡፡

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እና 13 መሰረት ለባለስልጣኑ መረጃ ያልቀረበበትን እና ስለምርቱ የንግድ ስም፣ ብራንድ፣ ወይም የንግድ ምልክት እንዲያውቀው ያልተደረገ ምርት ማምረት፣ ማስመጣት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው፡፡

3) ባለስልጣኑ ህገ-ወጥ ምርቶችን በየወቅቱ ለባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፤ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዳግባብነቱም የሚመለከተው አካል የአስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወስድ እና በወንጀል ተጠያቂ እንዲያደርግ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

4) ባለስልጣኑ አግባብነት ካለው አካል ጋር በመሆን ህጋዊ የትምባሆ ምርት ከህገ-ወጥ ምርት መለየት የሚቻልበትን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 13. ስለትምባሆ ምርት ማሳወቅና ለውጥ

1) ማንኛውም የትምባሆ አምራች ወይም አስመጪ የሚያመርተውን ወይም የሚያስመጣውን ምርት ይዘት፣ ስምና የንግድ ምልክት ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

2) ልዩ ፈቃድ ተሰጥቶት ያለ ሰው ያሳወቀውን የትምባሆ ምርት የንግድ ስም፣ የንግድ ምልክት፣ ይዘት፣ ቅርጽ፣ መሸጊያ ወይም ማንኛውም የተፈቀደ መረጃ ላይ ለውጥ ከማድረጉ በፊት ለባለስልጣኑ ማሳወቅና ማስፈቀድ አለበት፡፡

3) ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በአዲስ መለያ የትምባሆ ምርት ከማምረቱ ወይም ከማስመጣቱ በፊት ለባለስልጣኑ ማሳወቅና ማስፈቀድ አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት ለውጥ ለማድረግ የቀረበ ጥያቄን ባለስልጣኑ ለውጡ በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን በመመዘን የሚወስን ይሆናል፡፡

# ክፍል ሦስት

# ትምባሆን እና የትምባሆ ኢንዱስትሪ ማስተዋወቅ፣ ፕሮሞሽን እና ስፖንሰር ማድረግ

## 14. ትምባሆን ማስተዋወቅና ፕሮሞት ማድረግ

1) በአዋጁ አንቀጽ 61 ትምባሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማስተዋወቅ ክልከላ የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) በድምፅ፣ በምስል ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል የግንኙነት መንገዶች፣ በህትመት፣ በስዕል ወይም ሜልዕክት ለማስተላለፍ በሚቻል ማንኛውም መንገድ ትምባሆን፣ ስለትምባሆ ወይም የትምባሆ ኢንዱስትሪ ጽሑፍ ወይም ከትምባሆ ጋር ተያያዥ የሆነ ጉዳይን ማሳየት፣ መግለጽ ወይም ማጠቆም፤

ለ) በቴሌቪዥን፣ በሬድዮ፣ በስልክ፣ በማህበራዊ ትስስር ገጽ፣ በኢንተርኔት ወይም በማስል የግንኙነት ዘዴ ትምባሆን፣ የትምባሆ ኢንዱስትሪ ወይም ተያያዥ የሆነ ጉዳይን ማሳየት፣ መግለጽ ወይም ማጠቆም፤

ሐ) የትምባሆ ምርትን ወይም የትምባሆ ምልክትን ወይም ስዕልን ወይም ፎቶ ወይም ማናኛውም የትምባሆ ምርት ወይም የትምባሆ ኢንዱትሪ ገላጭ ሁኔታ በችርቻሮ ማሻጫ ቦታ፣ ለህዝብ ክፍት በሆነ ቦታ ወይም ስራ ቦታ ወይም በአገልግሎት ማስጫ ማስቀመጥ ወይም ማሳየት፤

መ) የዋጋ ቅናሽ እንዳለ መግለጽ፤

ሠ) የትምባሆ ምርት የብራንድ ስም፣ ማለያ፣ የንግድ ምልክት፣ የድርጅት አርማ፣ የንግድ ማለያ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማለያን የትምባሆ ምርት ካልሆኑ ሌሎች ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ጋር ማያያዝ ወይም ትምባሆ ነክ ያልሆኑ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን በተመሳሳይ መንገድ ከትምባሆ ምርት ወይም የትምባሆ ኢንዱስትሪ ጋር ቁርኝት ወይም ተያያዥነት እንዳላቸው መግለጽ ወይም ማሳየት፡፡

2) በአዋጁ አንቀጽ 61 ትምባሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ፕሮሞት ማድረግ ክልከላ የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) የትምባሆ ምርትን ወይም የትምባሆ ኢንዱስትሪ ስም ወይም ትምባሆ የተመለከተ ሜልዕክት፣ ፎቶ፣ ስዕል፣ መግለጫ ወይም ማስል ጉዳይ የያዘ እንደቁልፍ መያዣ፣ ቲሸርት፣ ኮፍያ፣ ዣንጥላ፣ ማለኮሻ ወይም ሌላ ማንኛውም ቁስ ከትምባሆ ጋር ወይም ለብቻው ለሰው ማስጠት፤

ለ) የድርጅቱን አርማ ወይም የትምባሆ ምልክት ያለው ወይም የድርጅቱ ማለያ ወይም የትምባሆ ምልክት ቢኖረውም ባይኖረውም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከትምባሆ ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ያለን ቁስ ማቅረብ ወይም ማስራጨት፤

ሐ) የገንዘብ ወይም የቁስ ስጦታ ማስጠት ወይም ማቅረብ፤

መ) ናሙናን ጨምሮ የትምባሆ ምርትን በነጻ ማቅረብ፤

ሠ) የትምባሆ ምርቶችን ለገዛ ሌሎች እቃዎችን የሚገዛበትን ነፃ ኩፖን ማስጠትን ጨምሮ ሌሎች ተመሳሳይ የምርቃት አይነት ተግባሮችን መፈፀም፤

ረ) የትምባሆ ምርት፣ ድርጅት ወይም ምርቱን ሊያስተዋውቁ የሚችሉ ቁሶች የተመለከተ መረጃን ማስተላለፍን ጨምሮ ትምባሆን ወይም ድርጅቱን በተመለከተ ቀጥታ ግለሰቦች ላይ በማነጣጠር ወይም በአጠቃላይ ለማህበረሰቡ ወይም ለተወሰኑ የማህበረሰብ አባላት ሜልዕክት ወይም ደብዳቤ መላክ፤

ሰ) የትምባሆ ምርትን፣ ድርጅትን ወይም ተጠቃሚነትን ፕሮሞት በሚያደርግ መንገድ የሸማቾች ቅኝት ወይም የገበያ ጥናት ማካሄድ ወይም ተመሳሳይ አይነት ስልት ማጠቀም፡፡

3) ህገ-ወጥ የትምባሆ ምርት መከላከል ወይም ሌላ ህጋዊ ጉዳይን በሚስታከክ የትምባሆ ምርትን ወይም የትምባሆ ኢንዱትሪን ማስተዋወቅ ወይም ፕሮሞት ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

4) የተወሰነ የትምባሆ ማጠን ያለውን ምርት ለሸጠ ማንኛውም ሰው ሽልማት ማስጠትን ጨምሮ የሽያጭ ማበረታቻ ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም ሽያጭን በሚያበረታታ መንገድ ለቸርቻሪዎች የሚደረግ ክፍያ ወይም ሌላ ዓይነት ድጋፍ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

5) የትምባሆ ምርት ማስታወቂያ በማስረጨት የተሳተፈ ሰው ሚዲያውን በሚቆጣጠርበት ሁኔታ ላይ ካለ የተከለከለውን ስርጭት የማስነሳት ወይም እንደአግባቡ ሚዲያው ወይም ስርጭቱ ተደራሽ እንዳይሆን ተገቢ የሆነ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

## 15. ስለተፈቀዱ የንግድ ሚዲያዎች

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 የተመለከተው ክልከላ ቢኖርም የሚከተሉት ሚዲያዎች የተፈቀዱ ናቸው፡፡
   ሀ) አግባብ ባለው ህግ መሰረት እና ወሰን መሰረት የትንባሆ ምርት የንግድ ምልክት፣ ብራንድ ስም፣ ምርት ስም እና የአምራች ስምን በትንባሆ ምርት ማሸጊያና ገላጭ ጽሑፍ ላይ ማሳየት፤
   ለ) በትንባሆ አምራች፣ አስመጪ፣ አከፋፋይ፣ ሻጭ ወይም እነዚህን በሚወክል ሌላ ሰው የተደረገ ምንም አይነት የገንዘብ ወይም የአይነት ክፍያ ሳይኖር በማናኛ ብዙሀን ላይ የትምባሆ ምርትን ወይም ትምባሆን ማጠቀም በተመለከተ በአጋጣሚ ወይም በታሪካዊ እውነታ ወይም ምክንያታዊ በሆነ የጋዜጠኝነት ወይም የስነ-ጥበብ ስራ ላይ ወይም ትምህርታዊ ለሆነ አላማ የሚደረግ ገለጻ፤
   ሐ) በትንባሆ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይ፣ ሻጭ ወይም እነዚህን በሚወክል ሌላ ሰው የተደረገ ምንም አይነት የገንዘብ ወይም የአይነት ክፍያ ሳይኖር የትምባሆ ምርትን ወይም ትምባሆን ማጠቀም በሚመለከት እውነተኛ የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ወይም ሳይናሳዊ አስተያየት፤
   መ) ለንግድ ስራ አስተዳደር ወይም የኮርፖሬሽን ሪፖርት ሚድረግ የሚባ እንደ የአካባቢ ጥበቃ፣ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮችን እና ማሰል በህግ የሚጠበቁ ጉዳዮችን ለሚመለከታቸው አካላት በትንባሆ ኢንዱስትሪ የሚሰራጭ ሚዲያ ወይም ሪፖርት፤
   ሠ) የንግድ ውሳኔ ለመወሰን ለማስቻል ዓላማ ለትምባሆ ነጋዴ የሚሰጥ ሚዲያ፤
   ረ) በትምባሆ ኢንዱስትሪው የሚዘጋጅና ተደራሽነቱ ለትምባሆ ኢንዱስትሪው ሰራተኞች፣ ኮንትራክተሮች፣ አቅራቢዎች እና ለሌሎች የትምባሆ ንግድ አጋሮቹ ብቻ የሆነ የዜና መጽሔት፡፡ በዚህ አግባብ የሚዘጋጅ የዜና መጽሔት ለእነዚህ አካላት ለግል ማጠቀሚያነት ከሚሆን ማጠን በላይ ማሰጠት፣ እንዲሁም ለሌሎች ሰዎች ተደራሽ እንዲሆን ሚድረግ የተከለከለ ነው፡፡
2) በንኡስ አንቀጽ (1) ፊደል (ረ) መሰረት በትምባሆ ኢንዱስትሪ የሚዘጋጅ የዜና መጽሔት እና በገዝዎቻቸው፣ ንግድ አጋሮች፣ በሰራተኞች ወይም ሸሪኮች መካከል የሚኖር የንግድ ግንኙነት ስለትምባሆ ምርቱ፣ ስለባህሪው፣ ስለመጣኛ እና ዋጋው፣ ስለምርቱ ምስል፣ ምርቱ ስለተሰራበት አካል እና ስለአስተሻሸጉ ትክክለኛውን ወይም እውነተኛውን ሚዲያ ከመግለጽ በስተቀር ማንኛውንም አይነት ሚዲያ መግለፅ የተከለከለ ነው፡፡
3) በንኡስ አንቀጽ (1) ፊደል (ሐ) መሰረት ገለጻ ሲደረግ ወይም ሲተላለፍ ትምባሆ ማጠቀም ጤናን እንደሚጎዳ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ሚልእክት ከፕሮግራሙ በፊት ማለጽ አለበት፡፡

### ክፍል አራት
### ለትምባሆ ጭስ ከመጋለጥ ስለማጠበቅ እና ስለትምባሆ ምርት ሽያጭ

## 16. ከትምባሆ ጭስ ነጻ ስለሚድረግ

1) ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 48 መሰረት ትምባሆ ሚጨስ እና ማጠቀም የተከለከለባቸውን ቦታዎችና አገልግሎቶች እንዳስፈላጊነቱ ከክልል ጤና ተቆጣጣሪ አካላት ጋር ተፈጻሚ መሆኑን ይከታተላል፤ እንዳስፈላጊነቱም ለክልሎች ድጋፍ ያደርጋል፡፡
2) በአዋጁ መሰረት ከትምባሆ ጭስ ነጻ መሆን የሚባባው ተቋም ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ፤ ባለስልጣኑ በራሱ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ሲኖሩ መወሰዱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ድርጅቱን የሚቆጣጠረው አካል ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድበት አስፈላጊውን ሚዲያ ይሰጣል፡፡
3) ማንኛውም ሰው ትምባሆ ሚጨስ ወይም ማጠቀም በተከለከለባቸው ስፍራዎች፣ ተቋማትና አገልግሎት መስጫ ለትምባሆ ሚጨሸ ወይም ማጠቀሚያ ቦታ ከልሎ ማዘጋጀት የተከለከለ ነው፡፡

## 17. ከትምባሆ ጭስ ነጻ የማድረግ ኃላፊነት እና የቁጥጥር ተግባር

1) በአዋጁ አንቀጽ 50 ከትምባሆ ነጻ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሰው፡ -

   ሀ) በአዋጁ አንቀጽ 48 ንኡስ አንቀጽ (1) ትምባሆ ማጨስ ወይም ማጠቀም በተከለከለበት ከበር ሚልስ ባለ ለህዝብ ክፍት የሆነ ቦታ እና ስራ ቦታ ወይም መጓጓዣ ማንኛውም ሰው እንዳይጠቀም ለመከልከል ትምባሆ ማጨስ ወይም ማጠቀም የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ በጉልህ የሚታይ ማስሰቢያ ከነባለቀለም ምልክት በግልጽ በሚታይ ቦታ ማለጠፍ እና ሰዎች ይህን ክልከላ በመተላለፍ ሊጠቀሙ ሲሞክሩ ማስቆም አለበት፤

   ለ) በአዋጁ አንቀጽ 48 ንኡስ አንቀጽ (2) ትምባሆ ማጨስ ወይም ማጠቀም በተከለከለበት ለህዝብ ክፍት በሆነ ቦታ ወይም ስራ ቦታ አስር ሜትር ዙሪያ ወስጥ ባለመግቢያ በር፣ ማከኮት፣ ወይም አየር ወደ ወስጥ ሊያስገባ በሚችል ሌላ ቦታ ትምባሆ ማጨስ ወይም ማጠቀም የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ በጉልህ የሚታይ ማስሰቢያ ከነባለቀለም ምልክት በእነዚህ ቦታ በግልጽ በሚታይ ሁኔታ ማለጠፍ እና ይህን በመተላለፍ ለማጠቀም ሚሞክር ሰው ማስቆም አለበት፤

   ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 48 ንኡስ አንቀጽ (3) ትምባሆ ማጨስ ወይም ማጠቀም በተከለከለባቸው ቦታዎች አስፈላጊ በሆኑ ከበር ሚልስ ቦታዎች፣ ቅጥር ግቢ ወስጥና ቅጥር ግቢ መግቢያ አከባቢ ትምባሆ ማጨስ ወይም ማጠቀም የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ በጉልህ የሚታይ ማስሰቢያ ከነባለቀለም ምልክት በግልጽ በሚታይ ቦታ ማለጠፍ እና ይህን በመተላለፍ ለማጠቀም ሚሞክር ሰው ማስቆም አለበት፤

   መ) ትምባሆ ማጨስ ወይም ማጠቀም በተከለከለበት ቦታ የእንግዳ ሚረፊያ አገልግሎት የሚሰጥ እንደሆነ በክፍሉ ወስጥ ትምባሆ ማጨስ ወይም ማጠቀም የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ ጽሑፍ ተጠቃሚው ሊያየው በሚችል ቦታ ማለጠፍ እና ይህን በመተላለፍ ለማጠቀም ሚሞክር ሰው ሲኖር ማስቆም አለበት፡፡

   ሠ) ከፊደል (ሀ) እስከ (መ) በተማለከቱት ሁኔታ ለማስቆም ሲሞክር ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ቢኖር፣ ኃላፊነት ያለበት ሰው ማጨስ በህግ የተከለከለና ተቋሙም ሆነ ተጠቃሚው በህግ እንደሚጠየቅ በመግለጽ አገልግሎቱን ማቋረጥና ቦታውን ለቆ እንዲወጣ ማድረግ አለበት፤

   ረ) የማስቆም ኃላፊነት ያለበት ሰው በፊደል (መ) ማሰረት አገልግሎቱን አቋርጦ እና ቦታውን ለቆ እንዲሄድ ጠይቆ ተጠቃሚው ፈቃደኛ ያልሆነለት እንደሆነ ለባለስልጣኑ፣ ለማንኛውም ጤና ተቆጣጣሪ አካል ወይም ለፖሊስ ማሳወቅ አለበት፤

   ሰ) የሲጋራ መተርኮሻ፣ አሽትሬይ ወይም ትምባሆ ለማጠቀም ወይም ተያያዥ አገልግሎት የሚሰጥ ምንም ዓይነት ቁስ እንዳይኖር ማድረግ አለበት፤

   ሸ) በተቋሙ ወይም በአገልግሎቱ የትምባሆ ማስታወቂያ፣ፕሮሞሽን ወይም ሽያጭ እንዳይከናወን መከላከልና እና ማስታወቂያ ወይም ፕሮሞሽን ሊሆኑ ሚችሉ ሚኘቸውም ጉዳዮችን ማስወገድ አለበት፡፡

2) የባለስልጣኑ ኢንስፔክተር ወይም ኃላፊነት ያለበት የጤና ተቆጣጣሪ በአዋጁ አንቀጽ 50 ኃላፊነት ያለበት ሰው ኃላፊነቱን በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ማሰረት እየተወጣ መሆኑን ሚረጋገጥ አለበት፡፡ በተለይም በአዋጁ አንቀጽ 48 የተጠቀሱት ቦታዎችና አገልግሎቶች ማጨስ ክልክል ነው ማስሰቢያ ያላቸው መሆኑን፣ የትምባሆ ሽያጭ የሌለ መሆኑን፣ ከትምባሆ ምርት ወይም ኢንዱስትሪ ማስታወቂያ ወይም ፕሮሞሽን ነጻ መሆናቸውን፣ ከሲጋራ ማከኮሻ፣ አሽትሬ፣ ወይም ማሰል ቁስ ነጻ መሆናቸውን፣ ከትምባሆ ሽታ ነጻ መሆናቸውን እና ማሰል የትምባሆ ቁጥጥር ስራዎችን ያረጋግጣል፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "**ከበር ሚልስ**" ማለት የተሰራበት ቁሳቁስ ዓይነት እና መዋቅሩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ መሆኑ ሳይወሰነው ማንኛውም በጣሪያ የተሸፈነ እና አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ግድግዳ ወይም መከለያ የተከለለ ስፍራ ሲሆን በረንዳን ጨምሯል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ፊደል (ለ) የተመለከተው አስር ሜትር ዙሪያ የሚለካው ከበር ሜለስ ጠርዝ ጀምሮ ወደ ከበር ውጭ ይሆናል፡፡

**18. ስለትምባሆ ምርት ሽያጭ**

1) በአዋጁ አንቀጽ 49 (1) መሰረት ዕድሜው 21 ዓመት ላልሞላው ሰው መሸጥ ወይም እንዲሸጥ ሚደረግ ክልከላ ተግባራዊ የሚሆነው የገዢውን ወይም የሻጭን ዕድሜ በአካላዊ ሁኔታ ወይም በመታወቂያ በሚረጋገጥ ይሆናል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ዕድሜን በአካላዊ ሁኔታ ማየት የሚቻለው ማንኛውም ሚበኛ ሰው የትምባሆ ሻጩ ወይም ገዢውን አካላዊ ሁኔታ በማየት በማያጠራጥር ሁኔታ ዕድሜው 21 ዓመት የሞላው መሆኑን ለመገመት የሚቻል ሲሆን ነው፡፡
3) በአካላዊ ሁኔታ በማያጠራጥር ሁኔታ ዕድሜውን ለማየት አስቸጋሪ ከሆነ፣ ዕድሜው መታወቂያውን በማየት ሚረጋገጥ አለበት፡፡

**19. ስለትምባሆ ምርት ማሸጊያ እና ምርት ቅርጽ ለውጥ**

የትምባሆ ምርት ተቀዳሚ ማሸጊያ ባለስልጣኑ በየወቅቱ የሚያወጣውን የጽሑፍና የምስል የጤና ማስጠንቀቂያ የያዘ ሆኖ፡-

1) በአንድ የማለያ ስም ወይም ምልክት (ብራንድ) የተለያዩ ቀለሞች ወይም ስሞች ወይም ቅርጽ በመጠቀም የትምባሆ ምርት ማምረት፣ ማስመጣት፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በባለስልጣኑ ፈቃድ በአንድ መለያ ወይም ብራንድ የተለያዩ ቀለሞችን ለመጠቀም ይቻላል፡፡ የተለያዩ ቀለሞችን መጠቀሙ የአዋጁን አንቀጽ 57 ንኡስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና አንቀጽ 61 ንኡስ አንቀጽ (1) ዓላማ የሚጻረር ዓይነት እንደሆነ ባለስልጣኑ መፍቀድ የለበትም፡፡ በዚህ ንኡስ አንቀጽ መሰረት ፈቃድ ተሰጥቶት ቀለሞቹ ጥቅም ላይ ወለው በሂደት እነዚህን የአዋጁን ድንጋጌዎች ዓላማ የሚቃረን ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆነ ባለስልጣኑ ፈቃዱን የሚሰረዝና ማጠቀም የሚከለከል ይሆናል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) መሰረት ቀለሞችን ለማጠቀም የሚፈልግ ሰው በቅድሚያ ለባለስልጣኑ የምርቱን ትክክለኛ ናሙና ማቅረብና ማስፈቀድ አለበት፡፡
4) ማንኛውም ሰው የትምባሆ ምርት የማሸጊያ ወይም የምርቱን አካላዊ ቅርጽ ለመቀየር በቅድሚያ ለባለስልጣኑ ትክክለኛ ናሙና ማቅረብና ማስፈቀድ አለበት፡፡ ባለስልጣኑ ጥያቄውን ሲመዝን ለወጡ የትምባሆ ምርቱን ሳቢ በማድረግ እና ተጠቃሚነት በማበረታታ የሚኖረውን ተጽኖ ከግምት ወስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡
5) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሰረት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በተገቢው ጊዜ ወስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

**20. የትምባሆ ኢንዱስትሪ ጣልቃ ገብነትን ስለመከላከል**

1) በመንግስት እና በትምባሆ ኢንዱስትሪ መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በጽሑፍ ሆኖ በህግ የተቀመጡ ገደቦችንና ክልከላዎችን ባከበረ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡
2) በተፈቀደ ሁኔታ ቢሆንም በመንግስት እና በትምባሆ ኢንዱስትሪ መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በማንኛውም መንገድ ትምባሆን ወይም የትምባሆ ኢንዱስትሪን የሚያስተዋውቅ፣ ወይም ፕሮሞት የሚያደርግ ወይም ተጠቃሚነት የሚያበረታታ መሆን የለበትም፡፡
3) በህግ እንዳይገለጹ የተከለከሉ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ በመንግስት እና በትምባሆ ኢንዱስትሪ መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ለማንኛውም ዜጋ ክፍት መሆን አለበት፡፡ ባለስልጣኑ ወይም ማንኛውም ሰው የእነዚህ ግንኙነቶች ቅጂ ሲጠይቅ መስጠት አለበት፡፡
4) የብሔራዊ የትምባሆ ቁጥጥር ጥምረት አባላት ተቋማቸው ከትምባሆ ኢንዱስትሪ ጋር ስለሚያደርጉት ግንኙነት የሚያወቁትን መረጃ ለባለስልጣኑ የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

5) ባለስልጣኑ የህግ ጥበቃ ያላቸው የንግድ ሚስጥሮች እንደተጠበቁ ሆነው የትምባሆ ኢንዱስትሪ እንቅስቃሴን እንዲሁም ጤናን የሚመለከቱ ገብነት በተመለከተ አስፈላጊ ሚስጥሮችን እንደአግባቡ ለህብረተሰቡ ይፋ ያደርጋል፡፡

6) በህግ ከሚፈቀዱ ክፍያዎች በስተቀር በትምባሆ ኢንዱስትሪ ለመንግስት የሚደረግ ማንኛውም የገንዘብ ወይም የዓይነት ስጦታ የተከለከለ ነው፡፡

7) የትምባሆ ኢንዱስትሪ በማንኛውም መንገድ የማህበራዊ ኃላፊነት ለመወጣት የገንዘብ ወይም የዓይነት አስተዋጽዖ ማድረግ፣ ለኩነት፣ ስብሰባ፣ ስልጠና፣ ወይም ማስል ዝግጅት እንዲካሄድ የገንዘብ ወይም የዓይነት ድጋፍ ማድረግ ወይም ባለሙያ መመደብ በአዋጁ አንቀጽ 51 ንኡስ አንቀጽ (5) መሰረት የተከለከለ ነው፡፡

## 21. የጥቅም ግጭትን ስለመከላከል

1) የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ በትምባሆ የንግድ ስራ ወስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው በማንኛውም ዓይነት የትምባሆ ቁጥጥር ተግባር ወስጥ ለመሳተፍ አይችልም፡፡

2) ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የትምባሆ ኢንዱስትሪ የደገፈው የጥናት ስራ ወስጥ ጥናቱን ለማከናወን ወይም ለማ ምገም ለመሳተፍ አይችልም፡፡

3) የመንግስት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ጥሰት የፈጸመ እንደሆነ የሚመለከተው ተቋም እና የፍትህ ተቋም አግባብነት ያለውን እርምጃ እንዲወስድ ባለስልጣኑ እና የክልል ጤና ተቆጣጣሪ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

## 22. ሪፖርት ስለማቅረብ

1) ማንኛውም የትምባሆ ኢንዱስትሪ በየዓመቱ ለባለስልጣኑ የስራ እንቅስቃሴውን የተመለከተ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቀርብ ሪፖርት ልዩ ፈቃድ የተሰጠበትን የስራ ዓይነት መሰረት በማድረግ፡ -

   ሀ) በሪፖርት ዓመቱ የተመረተ ምርት መጠን በጥቅል፣

   ለ) በሪፖርት ዓመቱ የተመረት ምርት መጠን በብራንድና በዓይነት ለይቶ፣

   ሐ) በሪፖርት ዓመቱ ከወጪ ወደ አገር ወስጥ የገባ ምርት ጠቅላላ መጠኑን በብራንድና በዓይነት ለይቶ፣

   መ) በሪፖርት ዓመቱ ወደ ውጭ አገር የተላከ ጠቅላላ መጠን በብራንድና በዓይነት ለይቶ፣

   ሠ) በሪፖርት ዓመቱ ከውጭ ወደ አገር ወስጥ የገባ፣ እና ከአገር ወስጥ የተገኘ ጥሬ ዕቃ፣ ጥቅም ላይ የዋለና ጥቅም ላይ ያልዋለው የጥሬ ዕቃ ዓይነትና መጠን፣

   ረ) በሪፖርት ዓመቱ ከአምራች ወይም አስመጪ ድርጅቱ ምርት ወይም ጥሬ ዕቃ በጅምላ የተረከቡ አከፋፋዮችና እያንዳንዱ አከፋፋይ ከድርጅቱ የወሰደው መጠን፣

   ሰ) ድርጅቱ ሪፖርቱን በሚያቀርብበት ወቅት ያለው የክምችት መጠን፣

   ሸ) አምራቹ ወይም አስመጪው ወይም ላኪው ምርቱ ሲሸጥበት የነበረው ዋጋ በምርት ዓይነት እና ብራንድ እና

   ቀ) ጅምላ አከፋፋይ ሲሆን ከአምራች እና አስመጪ የተረከበው መጠንና መሸጫ ዋጋ በምርት ዓይነት እና ብራንድ፤

   የያዘ መሆን አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚደረግ ሪፖርት በኢትዮጵያ በጀት ዓመት መዝጊያ ከሰኔ 15-30 ባለው ጊዜ ወስጥ ለባለስልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡

**ክፍል አምስት**

**የአስተዳደራዊ እርምጃ ስርዓት**

**23. ጠቅላላ**

1) በዚህ መመሪያ የተካተቱ ክልከላዎች በአዋጁ አንቀጽ 62 (7) የሚሆኑና አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰዱም በአዋጁ አንቀጽ 65፣ በዚህ መመሪያ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች ማስረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡
2) አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰደው የጥፋቱን ክብደት፣ የአፈጻጸሙ ሁኔታ እና ያደረሰውን ወይም ሊያደርስ ይችል የነበረውን የጉዳት ማጠን በማገናዘብ ይሆናል፡፡

**24. ስለአስተዳደራዊ እርምጃ**

1) በአዋጁ፣ በደንቡ ወይም በዚህ መመሪያ የተመለከተ ክልከላ ወይም ግዴታ ሆኖ ድርጊቱ በማንኛውም ህግ ወንጀል ሆኖ ያልተደነገገ እንደሆነ ክልከላውን በተላለፈው ሰው ላይ የሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ፡-
   ሀ) ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣
   ለ) ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያና በደንብ የሚወሰን መቀጮ
   ሐ) ለሶስተኛ ጊዜ ሲሆን ልዩ ፈቃዱን እስከ አንድ ዓመት ለሚሆን ጊዜ ማገድ፤
   መ) ለአራተኛ ጊዜ ሲሆን ልዩ ፈቃዱን ማስረዝ ይሆናል፡፡
2) ጥሰቱ በአዋጁ፣ በደንቡ ወይም በዚህ መመሪያ የተመለከተ ክልከላ ወይም ግዴታ ሆኖ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ እና ቅጣቱ ቀላል እስራት እንደሆነ ልዩ ፈቃዱ እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ይታገዳል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ማስረት ልዩ ፈቃዱ ታግዶበት የነበረ ሰው፤ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ ልዩ ፈቃዱ እስከ ሁለት ዓመት ለሚደርስ ጊዜ የሚታገድ እና በደንቡ ማስረት መቀጮ የሚጣልበት ይሆናል፡፡
4) ጥሰቱ በአዋጁ፣ በደንቡ ወይም በዚህ መመሪያ የተመለከተ ክልከላ ወይም ግዴታን ሆኖ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ እና ቅጣቱ ጽኑ እስራት እንደሆነ ወይም ልዩ ፈቃዱ ታግዶ የነበረ እንደሆነ ልዩ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡
5) በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ (1) እስከ (4) ባሉት ድንጋጌዎች የሚወሰዱት እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በትምባሆ ምርቱ ላይ እንዳግባብነቱ የመያዝ፣ የመውረስና የማስወገድ እርምጃዎች ሊወሰድ ይችላል፡፡
6) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የትምባሆ ምርቱ ወይም ጥሬ ዕቃው፡-
   ሀ) እንዲሸጥ ያልተፈቀደ፤
   ለ) ተፈጻሚ የጤና ማስጠንቀቂያ የሌለው፤
   ሐ) የተከለከለ ይዘት ያለው፤
   መ) ልዩ ፈቃድ በሌለው ወይም ልዩ ፈቃዱ ባልታደሰ ሰው የተመረተ፣ የተከማቸ፣ የተጓጓዘ፣ ለሽያጭ የቀረበ ወይም በማንኛውም ሁኔታ የቀረበ፤
   ሠ) ልዩ ፈቃዱ ታግዶ ባለበት ወቅት ከመታገዱ ወይም ማስረዙ በፊት በእጁ ይገኝ የነበረ ህግን የተከተለ ምርት ካልሆነ በስተቀር ልዩ ፈቃዱ በታገደበት ሰው እጅ የተገኘ፤
   ረ) በህገ-ወጥ መንገድ የተመረተ፣ ወደ አገር ወስጥ የገባ፣ የተከማቸ፣ የተጓጓዘ ወይም ገበያ ላይ የዋለ የትምባሆ ምርት የሚወረስና የሚወገድ ይሆናል፡፡
7) ልዩ ፈቃዱ ከመታገዱ ወይም ከማስረዙ በፊት በህጋዊ መንገድ የተገኘ ምርት በባለስልጣኑ ቁጥጥር እየተደረገበት በባለቤት ልዩ ፈቃድ ላለው ሰው ሊተላለፍ ወይም ሊሸጥ ወይም ሊወገድ ይችላል፡፡

**25. የትምባሆ ምርትን ስለመያዝ**

1) ማንኛውም የጤና ተቆጣጣሪ የትምባሆ ምርቱ ወይም ጥሬ ዕቃው በህገ-ወጥ መንገድ የተመረተ፣ ወደ አገር ወስጥ የገባ፣ ለገበያ የቀረበ፣ የተከማቸ፣ የተጓጓዘ ወይም በህግ የሚጠየቁ የጤና ማስጠንቀቂያ ወይም ሌሎች ማስፈርቶችን ያላሟላ ወይም ልዩ ፈቃድ በሌለው ወይም የታገድ ወይም የተሰረዝ ልዩ ፈቃድ ባለው ሰው እጅ የተገኘ ስለመሆኑ በበቂ ምክንያት የጠረጠረ እንደሆነ ምርቱን ለመያዝ ይችላል፡፡

2) በንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የተያዘ ምርት ተገቢው ውሳኔ እስኪሰጥ ተጠብቆ ይቆያል፡፡

26. ስለመውረስ

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት ወይም በአንቀጽ 25 መሰረት የተያዘ ምርት እንዳግባብነቱ እንዲወረስ ሊወስን ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ባለስልጣኑ ወሳኔ ከማሳለፉ በፊት በምርቱ ላይ መብት አለኝ የሚል ሰው ሀሳቡንና ማስረጃ እንዲያቀርብ እድል ማጠት አለበት፡፡

27. ስለማስወገድ

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የተወረሰ ምርት መወገድ አለበት፡፡

2) ባለስልጣኑ የተወረሰው ምርት አከባቢን በሚጎዳበት እና ተመልሶ ጥቅም ላይ ሊውል በሚችልበት ሁኔታ መወገዱን ሚረጋገጥ አለበት፡፡

28. በወንጀል ተጠየቂ ስለማስደረግ

የዚህ መመሪያ ድንጋጌን ጥሰት ሚፈጸም አግባብ ባለው ህግ የወንጀል ድርጊት ሆነው የተደነገገ እንደሆነ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ ከመወሰዱ በተጨማሪ የወንጀል ድርጊት የመመርመር ወይም መክሰስ ስልጣን ለተሰጠው ተቋም ተገቢውን ሚጃ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ስድስት
## የትምባሆ ቁጥጥር ብሄራዊ አስተባባሪ አካል

29. መቋቋም

1) በአዋጁ አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ (15) መሰረት የኢትዮጵያ የትምባሆ ቁጥጥር ብሄራዊ አስተባባሪ አካል (ከዚህ በኋላ "ብሄራዊ ጥምረት" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

2) የብሄራዊ ጥምረቱ ተጠሪነት ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ይሆናል፡፡

30. ዓላማ

የብሄራዊ ጥምረቱ ዓላማዎ -

1) በትምባሆ ቁጥጥር ላይ የወጣውን የዓለም ጤና ድርጅት የትምባሆ ቁጥጥር ማእቀፍ ኮንቬንሽን፣ የኮንቬንሽኑን አተገባበር መመሪያ እና አገሪቱ ያወጣቻውን የትምባሆ ቁጥጥር የህግ ማእቀፍ በፌደራል መንግስት ደረጃ ያለውን አፈጻጸም ማስተባበር፤

2) በተለያዩ የፌደራል መንግስት ተቋማት ያለውን የትምባሆ ቁጥጥርን ወጤታማነት መከታተል፤ እና

3) በፌደራል መንግስት አካላት፣ አጋሮችና ባለድርሻ አካላት መካከል የትምባሆ ቁጥጥር የትብብር ተግባራትን እና ትስስርን ማጠናከር፤

ነው፡፡

31. የብሔራዊ ጥምረቱ አባላት

1) የብሔራዊ ጥምረቱ አባላት፡ -

1. የኢትዮጵያ የምግብ፣ መድኃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን፤

2. የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት
3. የጤና ሚኒስቴር
4. የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
5. የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ
6. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
7. የገንዘብ ሚኒስቴር
8. የገቢዎች ሚኒስቴር
9. የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር
10. የግብርና ሚኒስቴር
11. የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
12. የትምህርት ሚኒስቴር
13. የትራንስፖርት ሚኒስቴር
14. የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
15. የግምሩክ ኮሚሽን
16. የኢ.ፌ.ዲ. ሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
17. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፖሊስ ኮሚሽን
18. የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን
19. የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
20. የአከባቢ፤ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን
21. የዓለም ጤና ድርጅት የኢትዮጵያ ጽህፈት ቤት
22. የሚቲዎስ ወንዱ የካንሰር ሶሳይቲ
23. መቋሚያ የማህበረሰብ ልማት ድርጅት
24. የጸረ-ወባ እና ልማት ማህበር እና
25. ሌሎች በባለስልጣኑ የሚሚጡ ተቋማት ናቸው፡፡

2) ባለስልጣኑ የጥምረቱ አባላት ተገቢውን ተሳትፎ እንዲያደርጉ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡
3) በንኡስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱትን ተቋማት በመወከል በጥምረቱ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው በትምባሆ ስራ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያልተሰማራ፣ ምንም ዓይነት የጥቅም ግንኙነት የሌለው እና ትምባሆ የማያጨስ ወይም የማይጠቀም መሆን አለበት፡፡

**32. *ሥልጣንና ተግባር***

የብሄራዊ ጥምረቱ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) የትምባሆ ቁጥጥር የህግ ማዕቀፎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ለገጠሙ ችግሮች የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ ለባለስልጣኑ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፤
2) የትምባሆ ቁጥጥር ተግባራት በጥምረቱ አባል ተቋማት መፈጸሙን ይከታተላል፣ይገመግማል፣ የልምድ ልውውጦች ያደርጋል፤
3) የትምባሆ ቁጥጥር የህግ ማዕቀፎች ስለሚጸድቁበት ለማረጋገጥ እንዲሁም አስፈላጊነቱ የማስከበር ቅኝት ያደርጋል፤
4) ለስራው አፈጻጸም የሚያግዙ የተለያዩ ንኡስ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ይቆጣጠራል፤
5) ህብረተሰቡ ስለትምባሆ ጎጂነት እና ክልከላዎች ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖረውና በመካላከሉ ላይ ተሳትፎ እንዲያደርግ የህብረተሰብ ንቅናቄ እንዲደረግ ያደርጋል፤
6) ለክልል የትምባሆ ቁጥጥር አስተባባሪ አካል ድጋፍ ያደርጋል፤

7) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናወናል፡፡

**33. የብሄራዊ ጥምረቱ አደረጃጀት**

የብሄራዊ ጥምረቱ፡ -

1) በባለስልጣኑ የሚወከል አንድ ሰብሳቢ፤
2) ጸሐፊ፣
3) አባላት፣ እና
4) እንዳስፈላጊነቱ ንዑስ-ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡

**34. የሰብሳቢ፣ ጸሐፊ እና አባላት ሀላፊነት**

1) የብሔራዊ ጥምረቱ ሰብሳቢ የጥምረቱን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ስብሰባዎችን ይመራል፣ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ በጥምረቱ ይሁንታ አግኝቶ በባለስልጣኑ ሲጸድቅ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፡፡
2) የብሔራዊ ጥምረቱ ጸሐፊ የስብሰባዎችን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ወይይቶችን ይዘግባል፣ የሚወሰኑ አቅጣጫዎች ለአባላት ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
3) የብሔራዊ ጥምረቱ አባላት ጥምረቱ ዓላማውን ሊያሳካ የሚችልበትን ጥረት ሁሉ ያደረጋሉ፤ ተቋማቱን የሚወክሉ ባለሙያዎች የትምባሆ ቁጥጥር ተግባራትን በተቋማቸው ያስተባብራሉ፡፡
4) በብሔራዊ ጥምረቱ የሚቋቋሙ ንኡሳን ኮሚቴዎች፤ የተቋቋሙበት ጉዳይን ያከናወናሉ፤ ለጥምረቱ ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡
5) የብሔራዊ ጥምረቱ የወስጥ አሰራሩን በተመለከተ ለራሱና በእርሱ ለተቋቋሙ ንኡሳን ኮሚቴዎች የአሰራር ስርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

**35. የብሄራዊ ጥምረቱ ስብሰባ**

1) ብሄራዊ ጥምረቱ በየሶስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ የሚኖረው ይሆናል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳቢው በማናቸውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
2) ከብሄራዊ ጥምረቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3) የብሄራዊ ጥምረቱ ወሳኔ የሚተላለፈው በአብለጫ ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል፡፡ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
4) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የብሄራዊ ጥምረቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ወስጠ ደንብ ያወጣል፡፡
5) ሁኔታው የሚጠይቅ ካልሆነ በስተቀር የብሄራዊ ጥምረቱ ስብሰባ በባለስልጣኑ ዋና ማስሪያ ቤት የሚከናወን ይሆናል፡፡

**36. የበጀት ምንጭ**

የብሄራዊ ጥምረቱ አስፈለጊ ወጪዎች በባለስልጣኑ እና አጋር ድርጅቶች የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**37. ስለንግድ ሰንሰለት**

1) በአገር ወስጥ የትምባሆ ምርት ወይም ጥሬ ዕቃ መግዛት ወይም መሸጥ የሚቻለው ከባለስልጣኑ የተሰጠ የጸና ልዩ ፈቃድ ካለው ወይም ላለው ሰው ብቻ ይሆናል፡፡
2) ከውጭ አገር የሚደረግ የትምባሆ ምርት ወይም ጥሬ ዕቃ ግዥ ከህጋዊ ምንጭ መሆን አለበት፡፡

**38. የአገልግሎት ክፍያ**

የአገልግሎት ክፍያ የሚጠየቅበት አገልግሎት ለማግኘት በቅድሚያ ክፍያ መክፈልና ለባለስልጣኑ ደረሰኝ መቅረብ አለበት፡፡

**39. ስለተሸረ ህግና በከፊል ተፈጻሚ የማይሆንባቸው ጉዳዮች**

1) የትምባሆ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 28/2007 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2) ከቀረጥ ነጻ በሆነ መንገድ ለዲፕሎማቶችና መብት ላላቸው ሰዎች በጀኔቫ ኮንቬንሽን ማሰረት በልዩ መንገድ የሚገቡ የትምባሆ ምርቶች በተፈቀደላቸው ቦታ እና ለተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ የሚቀርቡ ሆኖ የትምባሆ ጤና ማስጠንቀቂያ እና ገላጭ ጽሑፍ እንዲሁም ይዘትን በተመለከተ ይህ መመሪያ እና መመሪያ ቁጥር 45/2012 ተፈጻሚ አይሆንም፡
3) በንኡስ አንቀጽ (2) ማሰረት ወደ አገር ወስጥ የሚገቡ ምርቶች የስሪት አገር ያላቸዉን የጤና ማስጠንቀቂያ ይዘው እንዲገቡ ባለስልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**40. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከሚያዚያ 05 ቀን 2013 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ሄራን ገርባ**

**ዋና ዳይሬክተር**

**የኢትዮጵያ የምግብ እና መድኃኒት ባለስልጣን**

የትምባሆ ምርት ይዘትን ይፋ ማድረጊያ ቅጽ 1

የድርጅቱ ስም፡

የድርጅቱ የልዩ ፈቃድ ቁጥር…

ፈቃዱ የተሰጠበት ቀን…

የተሰማራበት የትምባሆ ንግድ ስራ ዓይነ __________ (ማምረት፣ ማስመጣት፣ በጅምላ ማከፋፈል)

- የምርት ዓይነት እና ይዘት ዝርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ይገለጽ፤

| የምርት ዓይነት | የብራንድ ዓይነት | በውስጡ ያለው የንጠረ ነገር ዓይነቶችና ማጠን | በውስጡ የያዛቸው ጎጂ ንጥረ-ነገሮች | የምርቱ ምንጭ (በአገር ውስጥ የሚሚረት፣ ከውጪ ) | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|
| ሲጋራ | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| ሲጋር | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| ሲጋሪሎስ | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| ፒፓ (በትቦ የሚጨስ ትምባሆ) | | | | | |
| ሱረት | | | | | |
| ሌላ የትምባሆ ምርት | | | | | |

ሚጃወን ያዘጋጀው ሰው ወይም ክፍል ሥም_______________________________

ፊርማ________________________________________

ቀን__________________________________________

ያጸደቀው አካል ሥም____________________________

ፊርማ________________________________________

ቀን____________________________________________